# የመከኑት ጬኸቶች !

ዋለ አምባዬ 7/20/12

በዚያን ሰሞን በአሜሪካን በተካሄደው የG-8 ሀገራት ስብሰባ ላይ በፕሬዚዳንት ኦባማ ጋባዥነት ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ተገኝተው በምግብ ዋስትና ላይ ንግግር እንዲያደርጉ ከቤኒን፣ ጋናና፣ ታንዛኒያ መሪዎች ጋር ተጋብዘው ነበር፡፡ ይኼኤም መቀመጫቸውን አሜሪካን ያደረጉት አምነስቲ፣ ሲፒጄ (የጋዜጠኞች መብት ተከላካይ ድርጅት) እንዲሁም የኦክላንድ ኢንስቲትዩትና ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የወዳጅነት ንቅናቄ ተብለው የሚጠሩ ድርጅቶች መግለጫዎችን በማውጣት ተቃውሟቸውን አሰምተው ኖሯል፡፡ ታዲያ ምን አዲስ ነገር ተፈጠረ? የሚለው ጥያቄ ይጭር ይሆናል፡፡ የተለመዱ ዓለም አቀፍ ጬኸቶችን መስማት እንግዳ ነገር ባይሆንም በዚህ ዙሪያ አንድ ማለትን መረጥኩ፡፡

አምነሲቲ የስብሰባ መብትን፣ ሲፒጄ የፕሬስ ነፃነትን፣ ኦክላንድ ኢንስቲትዩትና ለአዲሲቱ ኢትዮጵያ የወዳጅነት ንቅናቄ የተባሉት ድርጅቶች መሬት በውጭ ኢንቨስተሮች በብዛት እንዲያዝ በመደረጉ ከ70 ሺህ በላይ ዜጎች ከመሬታቸውና ከእርሻቸው መፈናቀልን፣ ሌሎች 150 ሺህ ሰዎች ደግሞ በሰፈራ ወደ ሌላ ቦታ የማዛወር እቅድ መኖሩን በመጠቃቀስ ክስ አቅርበዋል፡፡ ለዚህም ፕሬዚዳንት ኦባማ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስን በማነጋገር ጠንከር ያለ ግፊት እንዲደርጉ የሚጠይቁ ነበሩ፡፡

የሁሉም ድርጅቶች የመረጃ ምንጮች በሀገር ውስጥና በውጭ የሚገኙ የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮች፣ በተናጠልም ይሁን በቡድን የተደራጁ ግለሰቦች ናቸው፡፡ በኢሜልና በፋክስ በኢንተርኔት ጭምር በመጠቀም የተሰራጩት እነዚህ ሀሰተኛ መረጃዎች ከእውነታው ውጭ የተዛቡ፣ በግነት ላይ የተመረኮዙ መሆናቸውም ሌላው ጉዳይ ነው፡፡ ምንጮቹ ሀሰተኛ መረጃ በማቀበል የሀገሪቱን መልካም ገጽታ ጥላቻ ለመቀባት ሌት ተቀን የሚራወጡ መሆናቸው ደግሞ ሌላው አስገራሚ ጉዳይ ነው፡፡ የአምነስቲም ሆነ የሲፒጄ ተደጋጋሚና ለዓመታት የዘለቀ ውንጀላ አዲስ ነገር አይደለም፡፡ ከኦክላንድ ኢንስቲትዩት ጀርባ እነማን እንዳሉም ሚስጥር አይደለም፡፡

በአሁኑ ወቅት በጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ የሚመራው መንግስት ከዚህ ቀደም ከነበሩት መንግስታት ጋር ሲነጻጸር ታይቶና ተሰምቶ የማይታወቅ ከፍተኛ የመሰረተ ልማትና የምጣኔ ሀብት እድገት ማስመዝገቡን እነዚሁ ወገኖች ተቀበሉም አልተቀበሉም አይካድም፡፡

ኢትዮጵያ እንደ ሀገር እጅግ በጣም ጥንታዊ የታሪክና የስልጣኔ ባለቤት እንደነበረች ዓለም ያውቃል፡፡ በዓለም የመጀመሪያው የሰው ዘር መገኛ፤ የራሷ ፊደል፣ የቀንና ዓመት አቆጣጠር ያላት፤ የአክሱም ሥልጣኔና ሥርወ መንግስት ባለቤት፣ በዚያ ዘመን የራሷን መገበያያ ገንዘብ የቀረፀች፣ አነስተኛ እደ ጥበብ ያስፋፋች፣ ደመወዝተኛ ሰራዊት ያቆመች፣ የባህር ሃይል ባለቤት የነበረች፣ ከቀይባሕር አልፋ እስከ መካ መዲና ከየመን እስከ ሶማሌ በርበራ ድረስ ትገዛና ታስተዳድር የነበረች

ስለመሆኗ የውጭ ዜጎች ዋቢ ጠቅሰው የጻፏቸው ለቁጥር የሚያታክቱ መጽሐፍት ያሰረዳሉ፡፡ የነዛጉዌ ላስታ ሥርወ መንግስት፣ የጎንደር ቤተ መንግስት፣ የላሊበላ ውቅር አቢያተ ክርስቲያናት፣ የአክሱም ሀውልትና ሌሎችም ለኢትዮጵያ ጥንታዊ ማንነት ምስክሮች ናቸው፡፡ ቀድሞ የነበረው ጥንታዊ የኃያልነትና የገናናነት ሥልጣኔ ፈርሶ በውስጥ ግጭት፣ ብጥብጥና ጦርነት ደም መፋሰስ ተተካ፡፡ የውጭ ኃይሎችም ያለመታከት በተለየ መልኩ ጣልቃ በመግባት በኃይማኖት ስምና ሽፋን በስለላ በመሰማራት ሀገሪቷን ለማዳከም ቢቻልም ለመቀራመት ማሰኑ፣ ደከሙ፡፡

እነዚህ ድርጅቶች በስም ቢለያዩም በተግባር አንድ ናቸው፡፡ በኢትዮጵያ ላይ ያነጣጠሩት አጀንዳዎቻቸውም ወደ አንድ ግብ የሚያመሩ ናቸው፡፡ ይህም የውጭ ሃይሎችን በኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅም ላይ ያነጣጠረ ስውርና ድብቅ ፍላጎት አጉልቶ ያሳያል፡፡ ምዕራባውያኑ ይህን አይነት ጨዋታዎችን በተለያዩ መንግስታዊ ባልሆኑ ነገር ግን ለብሔራዊ ጥቅሞቻቸው ሲሉ በሚራወጡ ድርጅቶች አማካኝነት ሲያራምዱ እንደነበሩ ያለፉት 50 አመታት ታሪካቸው በገሀድ ያሳያል፡፡

ለእነሱ የማይመች ፖሊሲ ወይንም በእነሱ ፍላጎት ስር የማይመራ በራሱና በሕዝቡ የሚተማመን መንግስትና መሪ ሲያጋጥማቸው በተለያየ ደረጃ አለም አቀፍ ዘመቻ ይከፍቱበታል፡፡ እንዲህም ይላሉ፡፡ በዚያች አገር የሰብአዊ መብት ረገጣ ይካሄዳል፤ ተቃዋሚዎች ወደ እስር ቤት ይጋዛሉ፣ የመኖርና የመጻፍ ነጻነት የለም፤ የግሉ ፕሬስ ይታፈናል፤ ጋዜጠኞች ወደ እስር ቤት ይወሰዳሉ የሚሉ በመረጃ ያልተደገፉ ዘገባዎቻቸውን ያቀርባሉ፡፡

ይህ ብቻም አይደለም፡፡ የውጭ ኢንቨስተሮች በሀገሪቱ ሕግ መሰረት የተጠየቁትን አሟልተው ሲገቡና ስራ ሲጀምሩ የመሬት ወረራ ተካሄደ፡ ገበሬው ተፈናቀለ፤ ሰብአዊ መብት ተረገጠ በማለት በኢትዮጵያ ላይ ጫና ሊደረግ ይገባል ሲሉ ለፕሬዚዳንት ኦባማ የጻፉትን መግለጫና ጥያቄ ለሌሎች በርካታ መንግስታት፣ በአፍሪካም፣ በላቲን አሜሪካም ሆነ በመካከለኛው ምስራቅ ጭምር ሲያራምዱ ኖረዋል፡፡ እንግሊዝ፤ አሜሪካን፤ ፈረንሳይ፣ ጣሊያን፣ ካናዳ፣ ወይንም በሌሎች ምዕራባውያን ሀገሮች ስለሚደረገው የራሳቸው ጉድ የከፋ የሰብአዊ መብት ጥሰትና ዘረኛነት በጋዜጠኞች ላይ በሚደርስ ጫናና በደል፣ በረሀብና በሥራ አጥነት ስለሚንገላቱ በሚሊዮን ስለሚቆጠረው ሕዝብ ጉዳይ ምንም ትንፍሽ የሚሉት ወይም ያሉት ነገር የላቸውም፡፡

በሌላው ሀገር የውስጥ ጉዳይ ገብቶ ማቡካትና መፈትፈቱን፡ ሲመቻቸውም በየትኛውም መንገድ የራሴ በሚሏቸው ሰዎች አመጽ ቀስቅሰውም፣ አስቀስቅሰውም ሁከትም ሆነ ነውጥ ፈጥረው በሚቻላቸው መንገድ ሁሉ ወደ መንበረ ስልጣን ለማውጣት የማይቆፍሩት ጉድጓድ የማይፈነቅሉት ድንጋይ የለም፡፡ ይህም ለእነሱ ጥቅምና ፍላጎት የሚንበረከክ፣ እሺ ብሎ የሚገዛ እነሱ የወደዱትን ሁሉ በታዛዥነት ሊያደርግና ሊፈፅም የሚችል መሪና መንግስትን ብቻ ነው በየሀገሩ ማየት የሚፈቅዱት፡፡ አይሆንም፣ የለም፡ አንቀበልም በራሳችን መንገድ እንሄዳለን የሚሉት ሁሉ

የነአምነስቲ፣ የነሲፒጄና የሌሎችም ዓላማና የጥቃት ሰለባ ከመሆን አይድኑም፡፡ ለዚህም ዋናው መነሻቸው እኛን የማይቀበሉ ከሆነ ለጋሽና እርዳታ ሰጪ ሀገራት በመሆናችን እርዳታ መቀነስ ወይንም ማቆም አለብን የሚል  ነው፡፡ ይህም የሀገራትን ሉአላዊ መብትና ነጻነት በእጅጉ የሚጋፋ ተግባር ነው፡፡ በቅርቡ በመካከለኛው ምስራቅ የሆነውንና እየሆነ ያለውንም ልብ ይሏል፡፡

ዛሬ ኢትዮጵያ የያዘችው ፈርጀ ብዙ ትግል በሁሉም መስክ ብቁ ሆኖ መገኘትና ራስን በመቻል ከአለም አቀፍ ተረጂነት ነጻ የመውጣት ትግል ነው፡፡ ታሪክንና ክብርን ከሚያጎድፈው የድህነትና የተረጂነት፣ ተመፅዋችነት ምእራፍ የመላቀቅ ታላቅ ግብግብ ነው፡፡ በአጭሩ ከተመጽዋችነትና ከተረጅነት እስከመጨረሻው የመገላገልና የመላቀቅ ትግልን ከግብ ለማድረስ አሁንም ብርቱና ያላሰለሰ ትግል ይጠይቃል፡፡ የሰብአዊ መብት መከበርም ሆነ የግሉ ፕሬስ ነጻነት ማደግ በሂደትና እያደር እየጎለበተ የሚሄድ ራሱን የቻለ ክንዋኔ ነው፡፡ ሲጀመር ከነበረበት ዛሬ በሁሉም መስክ የተሻሉ ለውጦችና እድገቶች ተመዝግበዋል፡፡ ኢህአዴግ ወደ ስልጣን ሲመጣ በኢትዮጵያ ታሪክና ሕገ መንግስት የፕሬስ ነጻነት፣ የግል ፕሬስ የሚባል አልነበረም፡፡  ባሕሉም አልታየም፡፤ ዋስትና አግኝቶ ስራ የጀመረው በዚሁ መንግስት ነው፡፡

የግሉ ፕሬስ ከሕግና ከስርዓት በላይ እንዲፈነጭ፣ ትርምስና ሁከት እንዲፈጥር የብጥብጥ መቆስቆሻ እንዲሆን ስጋትና ሽብር እንዲሰፍን የውጭ ሀይሎች መሳሪያና መጠቀሚያ በመሆንና በገንዘብ በመታገዝ ሕዝብ ከሕዝብ ያጋጭ ያባላ የሚል ሕግ በየትኛውም ዓለም ላይ የለም፡፡ ይህን የሚያደርግ ጋዜጣም ጋዜጠኛውም በሕግ አይጠየቅም፣ አይዳኝም፡፡ ስርዓት አልበኛነት ይበረታታል የሚል ሕግ በእንግሊዝ ሆነ በአሜሪካ ምድር ላይ የትም ቦታ አልታየም፡፡ በሰብአዊ መብትና በፕሬስ ነጻነት ስም የኢትዮጵያን ሉአላዊነትም ሆነ ከድህነት ለመውጣት የጀመረችውን ታላቅ ትግል መድፈቅ እንደማይቻል ጋናዊው መሀመድ ኬይታም ሆነ አምነስቲ ኢንተርናሽናል፡ ኦክላንድ ኢንስቲትዩትም ሆነ ሌሎች በውል ይረዱታል ብለን እናምናለን፡፡ ለውጭ ኃይሎች ፍላጎት የሚንበረከክ፣ አጀንዳ እየተቀረፀለት በዚህ ግባ በዚህ ውጣ የሚባል መንግስት በኢትዮጵያ ታሪክ አልታየም፡፡

ኢትዮጵያ ከእርዳታ ተመጽዋችነት ከቅርብ የወደፊት አመታት በኋላ ራሷን ነጻ ታወጣለች፡፡ በግብርናው መስክ የሚታየው ታላቅ ተስፋ በምግብ እራስን ለመቻል ያበቃናል፡፡ ፕሬዚዳንት ኦባማ ስለኢትዮጵያ ግብርና የተናገሩት ማንም አስገዳጅ በሌላት የአለማችን ታላቋ ሀገር አሜሪካ የተሰጠ ምስክርነት ነው፡፡ ኢትዮጵያ አደገች ሲባል የሚጠሉ ኢትዮጵያውያንም አሉ፡፡ ጉድ ነው የሚያሰኘው ቁም ነገር ወሬ አይደለም፡፡ ጥላቻም አይደለም፡፡ ኢትዮጵያ በተግባር እየተለወጠች መሰረተ ልማቷ እያደገ እየሰፋ በትምህርት፣ በጤና፣ በኃይል ማመንጫ፤ በግድብ ግንባታ፤ በተፈጥሮ ማዕድንና በሌሎችም መስኮች የተረጋጋች ሀገር በመሆን ከፍተኛ የውጭ ኢንቨስትመንት መሳቧ፤ የቱሪስት ማዕከልነቷ፤ ለአፍሪካ ብቻ ሳይሆን ተመራጭ አፍሪካዊቷ የአለም መዲናና ማዕከል ወደ መሆን ማምራቷ፡ እያደገ የመጣው በዚህ መንግስት ነው፡፤  ይህቺን ሀገር ለመለወጥ ታላቅና ዘመን

የማይሽረውን ለትውልድ የሚሸጋገር ተግባር ስርቶአል፡፡ ስህተቶችም ቢኖሩ ለማረምና ለማስተካከል ያለውን ፈቃደኝነት በተደጋጋሚ አሳይቷል፡፡ የአምነስቲ ኢንተርናሽናል የሲፒጄ ተደጋጋሚ መግለጫዎች ማብቂያ የሌላቸውና ኢትዮጵያን ዒላማ ባደረገ ቋሚ አጀንዳነት የታቀዱ መሆናቸውን አይተናል፡፡ የእነዚህ ሃይሎች የተግባር ጩኸት ይቀጥላል፡፡ ኢትዮጵያ ወደ እድገት ምዕራፍ የጀመረችውን ፈጣን ጉዞ አጠናክራ ትገፋበታለች፡፡